“...ለሁሉም መማር ለሚፈልጉ።”

# የተማሪ የስነምግባር ደንብ

## የቆምነው ለእናንተ ነው

**የእኛ ተልዕኮ**
የኤሚሊ ግሪፍዝ ቴክኒክ ኮሌጅ ተልዕኮ
ተማሪዎች በሥራ ዓለም በተሳካ ሁኔታ
መወዳደር እንዲችሉ እና ራሳቸውን የቻሉ
ዜጎች እንዲሁም ዕድሜልክ መማራቸውን
የማያቋርጡ ተማሪዎችን ዕውቀት፣
ክህሎት እና አእምሮዋዊ ሃብት ማስጨበጥ
ነው።

**የእኛ ራዕይ**
የእኛ ራዕይ ለሥራው ዓለም የሰለጠነ
የተማረ እና ቴክኒክ የቀሰመ የሰው
ኃይል በአንደኛ ደረጃ የሚያፈራ
ምርጥ ኮሌጅ መሆን ነው።

**የእኛ እሴቶች**
ለላቀ ጥራት የቆምን ነን፣ ጥራት ያለው
የትምህርት ተቋም ግለሰቦችን እንደ
አመጣጣቸው እኩል ተቀብሎ ሁሉንም
ሊሆኑ የሚችሉትን በጣም የተሻለውን
ነገር እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ካለው
ፈጣን የቴክኖሎጂ ግስጋሴ ጋር አብረን
እየተጓዝን ለውጥ እና የፈጠራ ብቃት
አስፈላጊ በሆኑበት ቦታ ሁሉ ከማንም
ልቀን መሪ ሆነን እንገኛለን። በጣም
የተሻለውን የትምህርት መማሪያ ዕድል
በጣም በተሻለ የመማሪያ ድባብ
ለመስጠት የተቻለንን ጥረት ሁሉ
እናደርጋለን።


**ኤሚሊ ግሪፍዝ ቴክኒክ ኮሌጅ**
**1250 Welton Street**
**Denver, CO 80204**
**720-423-4700**
**EmilyGriffith.edu**


Emily Griffith TECHNICAL COLLEGE
• Opportunities For All Who Wish To Learn •

# የተማሪ የስነ ምግባር ደንብ

ኤምሊ ግሪፍዝ ቴክኒክ ኮሌጅ ደሕንነቱ የተጠበቀ፣ ለመማር አመቺ የሆነ እና ከማናቸውም አላስፈላጊ ረብሻ ነጻ የሆነ መማሪያቦታንማቅረብ ይፈልጋል። ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሠራተኞች ደሕንነት ወይም ሰላም አስጊ የሆነ ባሕሪ ወይም ትምህርት ቤቱ ለሌሎች ተማሪዎች የመማር ዕድል እንዳይሰጥ እንቅፋት የሚሆን ባሕሪ ተገቢነት እንደሌለው ባሕሪ ተደርጎይቆጠራል።

የተማሪ ስነ ምግባር ደንቡን የጣሱ ተማሪዎች፣አስተማሪውእና ተቆጣጣሪ አስተዳዳሪው ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ እስከሚወስዱ ድረስ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጡይደረጋል።

የሚከተሉት የደንብ ጥሰቶች ከትምህርት ቤት መባረር፣ ቃል ገብቶ ፈርሞ መመለስ፣ ወይም ወዲያውኑ ከትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የመሳሰሉ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ያስከትላሉ፥

ጸብ አጫሪ ባሕሪ ወይም በሠራተኞች፣ በተማሪዎች፣ በአጠቃላይ በሕዝቡ ላይ፣ በትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በትምህርት ቤቱ ይዞታ ሥር ባሉ ፋሲሊቲዎች ላይ አደጋ የማድረስ አዝማሚያ ማሳየት ወይም ማስፈራራት በጭራሽ በትዕግስት አይታለፍም።

በማናቸውም በኤምሊ ግሪፍዝ ቴክኒክ ኮሌጅ ይዞታ ሥር ባለ ፋሲሊቲ ወይም ተቋም ውስጥ ሽጉጥ፣ ጠበንጃ፣ ጥይት፣ የሚፈነዳ መሳሪያ ወይም በኮሎራዶ ሕግ መሰረት ሕገወጥ የሆነ የጦር መሳሪያ ማንም ሰውይዞ መገኘት አይችልም።

ድብድብ፣ ሰውን ማጥቃት፣ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ወሲባዊ ጥቃት።

በቃል ሰውን ማስቀየም፣ ማስፈራራት፣ ወይም መምህራንን፣ ተማሪዎችን ወይም ሠራተኞችን ማስፈራራት።

ሆን ብሎ የበላይ አካልን አለማክበር/ መጋፈጥ።

በኮሎራዶ እንደገና በተሻሻለው ሕግ፣ ክፍል 12-22-303 በተገለጸው መሰረት አልኮል መጠጥ፣ ሕገወጥ መድሃኒት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ማከፋፈል፣ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም ወይም ሰክሮ/ደንዝዞ መገኘት።

የነውጠኛ ሕገወጥ ቡድን ጋር የተገናኙ እንቅስቃሴዎች እና እንደየነውጠኛ ሕገወጥ ቡድን መገለጫ የሆኑ ቀለሞች፣ የእጅ ምልክቶች፣ የግድግዳ ጽሑፍ/ስዕሎች፣ ጌጣጌጦች፣ መዋቢያዎች፣ ማስታወሻ ደብተሮች፣ የንግድ ምልክቶች እና ሌሎች ማናቸውም መገለጫ ባሕሪያትን ይዞ መገኘት።

የትምህርት ቤት ንብረት ወይም የሌሎችን ንብረት ማበላሸት።

ቀጣፊነት፣ ማጭበርበር፣ የዕውቀት ስርቆት ወይም ሆን ብሎ የሐሰት መረጃ መስጠት።

አስመስሎ ማታለል፣ የትምህርት ቤት ሰነዶችን፣ ሪኮርዶችን፣ የማንነት መለያ ማቴሪያሎችን፣ የትምህርት መሳሪያዎችን እና የበይነ መረብ (ኢንተርኔት)መዳረሻን መለወጥ ወይም ከአግባቡ ውጪመጠቀም።

ስድ ወይም ብልግና ቋንቋ መጠቀም

ቁማር፣ ውርርድ ወይም በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ በማናቸውም ሁኔታ መወራረድ።

ያለፈቃድ ወደ ትምህርት ቤቱ መግባት እና /ወይም የትምህርት ቤቱን ንብረት መጠቀም

ያልተፈቀደለት የሽቀጦች ስርጭት ወይም ሽያጭወይም ያልተፈቀደ ነገር በትምህርት ቤት ማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም ግድግዳዎች ላይ መለጠፍ።

በማናቸውም የኤምሊ ግሪፍዝ ቴክኒክ ኮሌጅ ሕንጻዎች፣ የሥራ ቦታዎች ወይም በኤምሊ ግሪፍዝ ኮሌጅ ይዞታ ውስጥ ማጨስ።

ያለ መምህር ፈቃድ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምግብ ወይም የሚጠጣ ነገር ይዞ መምጣት ወይም መጠቀም።

ማናቸውም ባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪን በሕንጻውውስጥ ማቆም።

ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ መምጣት ወይም ልጆችን ለብቻቸው ወይም ያለ አዋቂ ክትትል በትምህርት ቤቱ ሜዳ ወይም መጫወቻ ቦታዎች ላይ ትቶ መሄድ።

ማናቸውንም እንስሳት ወደ ሕንጻውይዞ መምጣት። (በልዩ ሁኔታ የሚታለፉ ነገሮች፥ እንደ ዓይን እና እንደ ጆሮ

የሚያገለግል ውሻ። )

በሕንጻው ውስጥ ጓደኞች ማምጣት።
የጎብኚ ይለፍ ካርዶች የሚሰጡት
ወደፊት ተማሪ ሊሆኑ ለሚችሉ
ከአማካሪው ጋር ለመነጋገር ወይም
መማሪያ ክፍሎችን መጎብኘት ለሚፈልጉ
ብቻ ነው።

የጆሮ ማዳመጫ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣
ምልክት ማድረጊያ (ፔጀር)፣ ወይም
ተመሳሳይ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ
በትምህርት ጊዜ መጠቀም።

ቁምጣዎችን፣ ትከሻ ክፍት ልብሶች
(ሆልተርስ)ወይም ሌላ ማናቸውም
ገላን አጋልጦ የሚያሳይ ልብስን
ጨምሮ ማናቸውም ለመማር ማስተማሩ
ሂደት አዋኪ ሊሆን የሚችል ማናቸውም
ዓይነት አለባበስ።

ሌሎች በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት
ቤቶች የተማሪ ስነምግባር እና
ዲሲፕሊን ፖሊሲ ወይም ሌሎች
ተገቢነት ያላቸው በእያንዳንዱ
መማሪያ ክፍል ወይም ፕሮግራም የወጡ
ፖሊሲዎችን መጣስ።

*እነዚህ ፖሊሲዎች የወጡት
ለሁሉም ሰው ከፍተኛውን የመጠቀ
የመማር ድባብ ለማመቻቸት
እንዲቻል ተብሎ ነው።*